# አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ

## ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ ለመቀበል የወጣ ማስታወቂያ፣

ለአፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SIB/48/2019 (1stReplacement) እና በ24ኛው የኩባንያው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በፀደቀው የቦርድ ምልመላና የምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በ2018 ዓ.ም. የሚደረገው የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ የሚከናወነው፣ ምርጫውን ለማስፈፀም ህዳር 7 ቀን 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የኩባንያው 29ኛው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በተቋቋመው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት ነው።

በመሆኑም የቦርድ ጥቆማና አስመራጭ ኮሚቴ የተወዳዳሪ የቦርድ አባላትን ጥቆማ ለመቀበል ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ስለሆነ ባለአክሲዮኖች ለኩባንያው እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማድረግ ብቃት አላቸው ብለው የሚተማመኑባቸውን እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያመሟሉ እጩዎችን ከሰኔ 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ እጩዎችን እንድትጠቁሙ ኮሚቴው ይጋብዛል።

## ለምርጫ የሚጠቆሙ ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት የሚገቧቸው አነስተኛ መስፈርቶች፦

1. የአፍሪካ ኢንሹራንስ እ.ማ ባለአክሲዮን የሆነ/ች እና ዕድሜ 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች፤
2. በቦርድ አባልነት ለመስራት ፍቃደኛ የሆነ/የሆነች፣
3. ዕውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው/ላት ወይም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ/ች ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው/ላት፣
4. የዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቋሚው/ዋ የትምህርት ዝግጅት በመድህን፣ በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት እና በመሳሰሉት

ተመሳሳይ መስኮች አግባብነት ያለውና መሰረታዊ የሙያ ዕውቀት ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል (Preferable)፣

5. የቦርድ አባል ሆኖ ከተመረጠ/ች ለማገልገል በቂ ጊዜ፣ መልካም ስነምግባርና ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው/ያላት፣
6. ተጠቋሚው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ተቋም ከሆነ፤ ተቋሙን የሚወክለው የተፈጥሮ ሰው ማንነት በጥቆማው ቅጽ ላይ መገለፅ አለበት፣
7. አፍሪካ ኢንሹራንስ ኢ.ማ.ን ከዚህ በፊት በቦርድ አባልነት ለስድስት ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት (ለሁለትና ከዚያ በላይ የሥራ ዘመናት) አገልግሎ/ላ የለቀቀ/ች ከነበረ፣ ከቦርድ አባልነት ከለቀቀ/ች ስድስት ዓመት የሞላው/የሞላት፤ መሆኗን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
8. ለቦርድ አባልነት ከተመረጠች በኋላ ከመድህን ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስልጠናዎች ለመውስድ ፍቃደኛ የሆነ/ነች፣
9. የአፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ወይም የሌላ ኢንሹራንስ ኩባንያ ተቀጣሪ ስራተኛ ያልሆነ/ነች፤
10. የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኢ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ ኮሚቴ አባል ያልሆነ/ነች፣
11. በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በቦርድ አባልነት በማገልገል ላይ የማይገኝ/ትገኝ/፣
12. በራሱ ወይም በሚመራው ድርጅት ላይ የኪሳራነት ውሳኔ ያልተሰጠበት፤ ከታክስና ከባንክ ጋር የተያያዙ ግዴታዎቹን በአግባቡ የተወጣ/ታች፤ በማጭበርበር፤ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብ እና በመሳሰሉት ተከሶ/ሳ የፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የማያውቅ/ታውቅ፤
13. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሐራጅ ያልተሸጠበት፤ተከሶ ያልተፈረደበት ወይም የቦርድ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም የበላይ ሀላፊ በመሆን የሚመራው ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ብድር ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብደር ደረጃ ያልዞረበት(NPL)፤

❖ <u>ማሳሰቢያ፡-</u>

1. እያንዳንዱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን እስከ ዘጠኝ (9) የሚሆን እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መጠቆም ሲችል፣ እያንዳንዱ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነ ባለአክሲዮን ደግሞ እስከ ስድስት (6) የሚደርሱ እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መጠቆም ይችላል፡፡

2. መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴት እጩዎች ይበረታታሉ::
3. ጥቆማው በውክልና የቀረበ ከሆነ ውክልናው ጥቆማውን ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ የውክልና ፎቶ ኮፒው ከመጠቆሚያ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት::
4. ጠቋሚው ግለሰብ ወይም ማህበር/ድርጅት የተጠቋሚውን ፈቃደኝነት አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት::
5. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተወዳዳሪዎችን መጠቆም የምትፈልጉ ባለአክሲዮኖች ለጥቆማ የተዘጋጀውን ቅፅ ቦሌ ሩዋንዳ ከሚገኝበት አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ዋና መ/ቤት 12ኛ እና 11ኛ ፎቅ ቦርድ ጽ/ቤት ወይም ከኩባንያው ቅርንጫፎች ወይም ከአፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ድረ ገጽ https://africainsurance.com ላይ ማግኘት ይቻላል::
6. የመጠቆሚያ ቅጹ በአግባቡ ተሞልቶና ተፈርሞበት፣ ጠቋሚው ማህበር/ድርጅት ከሆነ ደግሞ ማህተም ተደርጎበት ቦሌ ሩዋንዳ ከሚገኝበት አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ዋና መ/ቤት 12ኛ እና 11ኛ ፎቅ ቦርድ ጽ/ቤት ወይም በኩባንያው ቅርንጫፎች በግንባር በመቅረብ የሞሉትን ቅጽ ማስረክብ ወይም በአፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ. ፖ.ሳ.ቁ. 12941 መላክ ይቻላል::
7. ከመስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም. በኂላ የሚቀርቡ ወይም የሚደርሱ ጥቆማዎች ተቀባይነት የላቸውም::
8. ለጥያቄና ተጨማሪ መረጃ በኮሚቴው ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ወይም በ0911 075575 እና 0911227749 ላይ በመደወል ማብራሪያ ማግኘት ይቻላል::

**የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኢ.ማ.**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማና ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ**